የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.6
ADDIS ABABA 13th December, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፪ሺ፲፭

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ…………………………………….ገጽ ፲፬ሺ፭፻፺

## Content

Regulation No. 527/2022

The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation ……........................................................Page 14590

**ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፪ሺ፲፭**

## <u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፩፻፫ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፪ሺ፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ወስጥ፡-

፩/ **“የግብርና ምርምር”** ማለት የዕጽዋት፣ የእንስሳት፣ አፈርና ውኃ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚከናወን ሳይንሳዊ ተግባር ነው፤

**Regulation No. 527/2022**

## THE ETHIOPIAN INSTITUTE OF AGRICULTURAL RESEARCH ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2023.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as “ The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation Number 527/2022”

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ **“Agricultural research”** means an undertaking to advance production, productivity and quality products in the areas of plants, animals, and soil and water resources in a sustainable manner;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ **"የግብርና ምርምር ሥርዓት"** ማለት በአገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርምር የተሰማሩ ተቋማት በጋራ ወይም በጣምራ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር በሚያገናኙዋቸው ጉዳዮች ላይ የሚመሰርቱት የተዋረድ ወይም የጎንዮሽ ግንኙነት ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚመሩበትን መርሆዎች እና አሰራሮችን የሚያካትት ነው፤

፫/ **"የግብርና ምርምር ማዕከል"** ማለት በፌደራል መንግሥት ወይም በክልል መስተዳድር የሚተዳደር ሆኖ ሥነ-ምህዳርን ወይም የማሕበረሰብ ተደራሽነትን ወይም የግብርና ምርት ዓይነትን ወይም የትኩረት መስክን ታሳቢ አድርጎ የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም የግብርና ምርምር ተግባራትን የሚያከናውን አካል ነው፤

፬/ **"ቴክኖሎጂ"** ማለት አዲስ ወይም የተሻሻለ ወይም የተላመደ የግብርና ምርት ዓይነት፣ አመራረትና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተጣመረ ዕውቀት፣ የድርጊት ጥበብ፣ የአሰራር ዘዴና ሥርዓት ሆኖ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ማነቆዎችን ለመፍታትና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችል ወይም ለዚህ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው፤

፭/ **"ዕውቀት"** ማለት በጥናትና ምርምር የሚገኝ ቴክኒክ፣ ክህሎት፣ ዘዴ፣ ጥበብን እና የአሰራር ሂደቶችን የሚያጠቃልል ሆኖ አንድን የግብርና ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ወይም የምርምር ዓላማን ለማሳካት የሚያስችል ጽንሰ ሃሳብ ነው፤

፮/ **"ማስተባበር"** ማለት የአገራዊ የግብርና ምርምር ስራዎች በቅንጅት፣ በትብብርና በውጤታማነት እንዲከናወኑ የማሳለጥ ተግባር ነው፤

2/ **"National Agricultural Research System"** means a collection of institutions engaged in the agricultural research within the country and doing research in harmony or in collaboration, having vertical or horizontal relationships with governing principles and working modalities;

3/ **"Agricultural Research Center"** means an agricultural research organ entirely dedicated in implementing research activities and projects; established or to be established or administered by Federal or Regional government to address agro-ecologies, social groups, or strategic commodities or strategic themes;

4/ "**Technology**" means new or improved or adapted product type and knowledge in agriculture that embedded with the provision of production and services, wisdom, working method and system that could solve the social and economic bottlenecks and improve the living conditions of the farming society or contributing to these;

5/ "**Knowledge**" means the sum of techniques, skills, methods, wisdoms and processes to be employed in the production of goods or services or in the accomplishment of objectives, such as scientific investigations;

6/ "**Coordination**" Means facilitating agricultural research endeavorsare conducted collaboratively to enhance efficiency and synergy;

፯/ "**አገልግሎት**" ማለት በኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ማንኛውም የስልጠና፣ የማማከርና ጥናት፣ የቤተ-ሙከራ ናሙና ፍተሻና ትንተና፣ በመስክና በቤተ-ሙከራ የቴክኖሎጂ ውጤታማነት ማረጋገጥ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በውል አማካይነት የሚከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፤

፰/ "**ተቋም**" ማለት የግብርና ምርምርን እንዲያካሂድ በሕግ የተፈቀደለት የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት አካል ወይም መንግስታዊ የልማት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

፱/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፩/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>መቋቋም</u>

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌደራል አስፈፃሚ ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**7/** "**Service**" means the provision of training, consultancy, laboratory testing, validating technologies in laboratories and under field conditions, and other similar activities that emanate from the competences of the institute or its missions that may be provided on contractual basis;

**8/** "**Institution**" means any Organization authorized to work on agricultural research at federal or regional level, at Universities or Colleges or government or private entities;

**9/** **"Region"** means any state established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and including the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrations;

**10/** "Ministry or Minister" means the Ministry of Agriculture or the Minister, respectively;

**11/** "**Person**" means physical or juridical person;

**12/** Any expression in masculine gender includes the feminine

## 3. <u>Establishment</u>

The Ethiopian Institute of Agricultural Research (hereinafter the "Institute'') is hereby established as a Federal Government Institution.

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ሥፍራዎች የግብርና ምርምር ማዕከላት ይኖሩታል፡፡

## ፭. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት እና በተጠቃሚዎች ፍላጎቶች ላይ ያተኩሩ በዕጽዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈርና ውኃ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና ዕውቀቶችን ማፍለቅ፣ ማሻሻልና ማላመድ፤

፪/ የግብርና ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ እና የመነሻ ቴክኖሎጂዎችን አባዝቶ ማቅረብ፤

፫/ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን ለማዘመን እና ውጤታማ ለማድረግ አቅም መገንባት፣

## ፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት የግብርና ምርምር ያከናውናል እንዲሁም እንዲከናወን ያደርጋል፤

፪/ ከአገራዊ የግብርና ልማት ፖሊሲ ጋር የተጣጣሙ የግብርና ምርምር ስትራቴጅዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፫/ ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ እና ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተባብራል፤

## 4. Head Office

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may have agricultural research centers elsewhere , as deemed necessary.

## 5. Objectives

The Institute shall have the following objectives:

1/ Generate, improve and adapt agricultural technologies and knowledge on plants, animals, soil and water addressing the needs of the agricultural development and the end users;

2/ Demonstrate agricultural research findings for users, multiply and provide source technologies;

3/ capacity building to Modernize and improve efficiency and effectiveness of the national agricultural research system.

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the following powers and duties to:

1/ Undertake and coordinate to undertake agricultural research in accordance with the national agricultural development policy and strategies;

2/ In harmonization with the National Agricultural Development Policy, develop the agricultural research strategies, programs and projects, and follow up the implementation of these;

3/ Establish and coordinate a system to develop and evaluate agricultural research programs and projects that meet the required national development needs;

፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ለሚቀርቡ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የመነሻ ቴክኖሎጅ ብዜት ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲባዛ ያደርጋል፤ ሂደቱንም ያስተባብራል፤

፭/ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ያማክራል፤

፮/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ በፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ገቢራዊ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፯/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ በማስፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ አመች በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የአህዝቦት ተግባር ያከናውናል፤

፰/ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የተመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ በመረጃ ቋት ያከማቻል፣ ያሰራጫል፣ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት ይገነባል፣ ይመራል፤

፱/ በግብርና ምርምር ተቋማትና የምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፲/ በግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት አቅም የማሳደግና የመገንባት ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ Establish a system for the production of source technologies, of improved Agricultural technologies provided by Agricultural research bodies multiply the source technologies and coordinate the process;

5/ Advise the government on agricultural research and development related policy issues;

6/ In collaboration with relevant stakeholders, establish functional system for creating strong partnerships among federal agricultural research centers and users for effective use of agricultural research technologies and follow up the implementation of it;

7/ In collaboration with relevant stakeholders, demonstrate research outputs through convenient and effective communication media and local languages to enhance the agricultural knowledge base of the public;

8/ Collect, collate, store and disseminate data and information related to agricultural research that are generated by the national research system and elsewhere, and establish a system for agricultural research data or information exchange mechanism;

9/ Organize functional platforms for promoting strong linkages among agricultural research institutions, consumers, and other value chain actors;.

10/ Design the development and upgrading of skilled and qualified human resources engaged in agricultural research; formulate and implement effective strategies to develop and build up human capacity;

፲፩/ የግብርና ምርምር ተቋማት ዘመናዊ የምርምር መሠረተ ልማትን እና የምርምር መሣሪያዎች ሳይንሳዊ ደረጃን የጠበቁ እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤ የምርምር ሥርዓቱ አካላት በቅንጅት የሚጠቀሙበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፪/ በሥሩ የሚተዳደሩ የግብርና ምርምር ማዕከላት እንደገና እንዲደራጁ፣ እንዲታጠፉ እና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ማዕከላት እንዲቋቋሙ የሚያስችል ጥናት በማድረግ በሚኒስቴሩ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ የግብርና ምርምር ማዕከላትን በብቃት ደረጃ መለኪያ መስፈርቶች መሰረት ያስገመግማል፣ የልህቀት ማዕከልነት ዕውቅና እንዲሰጥ ያመቻቻል፤

፲፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ጠቃሚ ውጤቶችን ላስመዘገቡ ሰዎች ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፭/ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አገራዊ ድርጅቶች ጋር ስትራቴጅካዊ አጋርነት ይመሰርታል፣ ስምምነቶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲፮/ በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያ ማህበራት ያበረታታል እንዲሁም ለግብርና ምርምር በመረጃ ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፯/ የግብርና ምርምር በሚያከናውኑ ተቋማት መካከል አስፈላጊ ያልሆነ የምርምር ድግግሞሽን በማስቀረት የምርምር ሥርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

11/ Establish an effective and efficient research infrastructures and equipment in conformity with scientific and international standards; create mechanisms to utilize the same resources by the agricultural research system collaboratively;

12/ Reorganize or dissolve any research center under the institute and establish new ones as deemed necessary through conduct study and implement as approved by the government;

13/ Based on standard quality measurement criteria's, it works to certify the competence of research centers in the national agricultural research system, and facilitate for excellence of research centers;

14/ Establish an award and recognition system to individuals or entities for meritorious achievements in the national agricultural research system;

15/ establish strategic partnership with relevant international and regional Agricultural research institutes and national Organizations having similar objective, signs agreements and implement thereof;

16/ Encourage agricultural professional associations and facilitate their contribution for the exchange of agricultural research knowledge and information;

17/ Establish a workable system to minimize duplication of research efforts thereby enhance efficiency and effectiveness of the agricultural research system;

፲፰/ የግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ምርምር ማካሄድ ለሚፈልጉ የአገር ውስጥና የውጭ የምርምር ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግብርና ምርምር ለማካሄድ የሚያስችል ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፱/ ከምርምር ሥርዓቱ ለሚወጡና የላቀ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ቴክኖሎጂዎች እና ዕውቀቶች የአዕምሮአዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

፳፩/ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችሉ ተቋማዊ የአፈፃፀም መለኪያዎችና አሰራሮችን ያዘጋጃል፤

፳፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፳፫/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተር፤

፪/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰. <u>የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ኢንስቲትዩቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

18/ Support foreign and local research institutions and individuals intending to undertake agricultural research in line with agricultural policies and strategies of the country;

19/ Facilitate the acquisition of ownership of intellectual property rights for technologies, knowledge, process and information generated by the agricultural research system;

20/ Collect service fee based on a rate set by a Regulation to be issued by Council of Ministers.

21/ Prepare institutional implementation standardes and practices that would help to implement its mission.

22/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

23/ Perform other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

## 7. <u>Organizational Structure</u>

The institute shall have:

1/ A Director General;

2/ Deputy Director Generals as required; and

3/ Necessary staffs.

## 8. <u>Powers and Duties of the Director General</u>

The Director General shall have the following powers and duties:

1/ The Director General shall be the Chief Executive Officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute;

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ሥር የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትን የፕሮግራምና የፕሮጀክት አፈጻጸም፤ የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤

ሐ) አግባብነት ባላቸው በፌደራል መንግሥት የሠራተኞች ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶና አጠናቅሮ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በጸደቀው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ለምርምር ማዕከላት እና በቅንጅት ለሚሰሩ ስራዎች ይመድባል፤ የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፡

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስፈላጊነቱ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2/ Without limiting the generality provided in Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Implement the powers and responsibilities of the Institute provided in Article 6 of this Regulation;

b) Supervise and follow up the implementation of programs and projects as well as the utilization of finance by the federal agricultural research centers;

c) Recruit and administer staff of the institute based on the Civil Service Laws of the Country;

d) Prepare, consolidate and submit the work program and budget of the institute to the government and follow up its proper implementation when approved;

e) Allocate budget to research centers based on the approved budget of the institute and follow up the utilization of the allocated fund for the intended activity;

f) Represent the institute in its dealings with third parties;

g) Consolidate the performance and financial report of the institute, and submit to the Ministry.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

## ፱. የምክትል ዋና ዳሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፲. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

## ፲፩. ስለሂሣብ መዝገብ

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብቱን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡

## ፲፪. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 9. Powers and Duties of the Deputy Director General

The Deputy Director General shall have the following powers and duties:

1/ Assist the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the activities of the institute;

2/ Execute other duties specifically assigned by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise , the Senior Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence

## 10. Budget of the Institute

The budget of the Institute shall be allocated by the Government.

## 11. Book of Accounts

1/ The Institute shall keep a complete and an accurate book of accounts.

2/ The Institute book of accounts shall be audited at least once a year by the Auditor General or by another Auditor designated by him.

## 12. Inapplicable Laws

Any other Regulations, Directives or Customary Practices which are in contradiction with this Regulation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

**፲፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**13. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette

**Done at Addis Ababa, on this 13th day of December, /2022**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.6
ADDIS ABABA 13th December, 2022

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፳፻፲፭

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ……………………………………..ገጽ ፲፬ሺ፭፻፺

**Content**

Regulation No. 527/2022

The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation ……........................................................Page 14590

**ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፳፻፲፭**

**የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፳፻፲፬ አንቀጽ ፩፻፫ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፳፻፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ወስጥ፡-

፩/ **“የግብርና ምርምር”** ማለት የዕጽዋት፣ የእንስሳት፣ አፈርና ውኃ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚከናወን ሳይንሳዊ ተግባር ነው፤

**Regulation No. 527/2022**

**THE ETHIOPIAN INSTITUTE OF AGRICULTURAL RESEARCH ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2023.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as “ The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation Number 527/2022”

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ **“Agricultural research”** means an undertaking to advance production, productivity and quality products in the areas of plants, animals, and soil and water resources in a sustainable manner;

፪/ **“የግብርና ምርምር ሥርዓት”** ማለት በአገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርምር የተሰማሩ ተቋማት በጋራ ወይም በጣምራ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር በሚያገናኙዋቸው ጉዳዮች ላይ የሚመሰርቱት የተዋረድ ወይም የጎንዮሽ ግንኙነት ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚመሩበትን መርሆዎች እና አሰራሮችን የሚያካትት ነው፤

፫/ **“የግብርና ምርምር ማዕከል”** ማለት በፌደራል መንግሥት ወይም በክልል መስተዳድር የሚተዳደር ሆኖ ሥነ-ምህዳርን ወይም የማሕበረሰብ ተደራሽነትን ወይም የግብርና ምርት ዓይነትን ወይም የትኩረት መስክን ታሳቢ አድርጎ የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም የግብርና ምርምር ተግባራትን የሚያከናውን አካል ነው፤

፬/ **"ቴክኖሎጂ"** ማለት አዲስ ወይም የተሻሻለ ወይም የተላመደ የግብርና ምርት ዓይነት፣ አመራረትና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተጣመረ ዕውቀት፣ የድርጊት ጥበብ፣ የአሰራር ዘዴና ሥርዓት ሆኖ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ማነቆዎችን ለመፍታትና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችል ወይም ለዚህ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው፤

፭/ **“ዕውቀት”** ማለት በጥናትና ምርምር የሚገኝ ቴክኒክ፣ ክህሎት፣ ዘዴ፣ ጥበብን እና የአሰራር ሂደቶችን የሚያጠቃልል ሆኖ አንድን የግብርና ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ወይም የምርምር ዓላማን ለማሳካት የሚያስችል ጽንሰ ሃሳብ ነው፤

፮/ **“ማስተባበር”** ማለት የአገራዊ የግብርና ምርምር ስራዎች በቅንጅት፣ በትብብርና በውጤታማነት እንዲከናወኑ የማሳለጥ ተግባር ነው፤

2/ **“National Agricultural Research System”** means a collection of institutions engaged in the agricultural research within the country and doing research in harmony or in collaboration, having vertical or horizontal relationships with governing principles and working modalities;

3/ **"Agricultural Research Center"** means an agricultural research organ entirely dedicated in implementing research activities and projects; established or to be established or administered by Federal or Regional government to address agro-ecologies, social groups, or strategic commodities or strategic themes;

4/ “**Technology**” means new or improved or adapted product type and knowledge in agriculture that embedded with the provision of production and services, wisdom, working method and system that could solve the social and economic bottlenecks and improve the living conditions of the farming society or contributing to these;

5/ “**Knowledge**” means the sum of techniques, skills, methods, wisdoms and processes to be employed in the production of goods or services or in the accomplishment of objectives, such as scientific investigations;

6/ “**Coordination**” Means facilitating agricultural research endeavorsare conducted collaboratively to enhance efficiency and synergy;

፯/ "**አገልግሎት**" ማለት በኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ማንኛውም የስልጠና፣ የማማከርና ጥናት፣ የቤተ-ሙከራ ናሙና ፍተሻና ትንተና፣ በመስክና በቤተ-ሙከራ የቴክኖሎጂ ውጤታማነት ማረጋገጥ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በውል አማካይነት የሚከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፤

7/ "**Service**" means the provision of training, consultancy, laboratory testing, validating technologies in laboratories and under field conditions, and other similar activities that emanate from the competences of the institute or its missions that may be provided on contractual basis;

፰/ "**ተቋም**" ማለት የግብርና ምርምርን እንዲያካሂድ በሕግ የተፈቀደለት የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት አካል ወይም መንግስታዊ የልማት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

8/ "**Institution**" means any Organization authorized to work on agricultural research at federal or regional level, at Universities or Colleges or government or private entities;

፱/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

9/ **"Region"** means any state established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and including the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrations;

፲/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

10/ "Ministry or Minister" means the Ministry of Agriculture or the Minister, respectively;

፲፩/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

11/ "**Person**" means physical or juridical person;

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

12/ Any expression in masculine gender includes the feminine

## ፫. <u>መቋቋም</u>

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌደራል አስፈፃሚ ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## 3. <u>Establishment</u>

The Ethiopian Institute of Agricultural Research (hereinafter the "Institute'') is hereby established as a Federal Government Institution.

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ሥፍራዎች የግብርና ምርምር ማዕከላት ይኖሩታል፡፡

## ፭. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት እና በተጠቃሚዎች ፍላጎቶች ላይ ያተኮሩ በዕጽዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈርና ውኃ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና ዕውቀቶችን ማፍለቅ፣ ማሻሻልና ማላመድ፤

፪/ የግብርና ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ እና የመነሻ ቴክኖሎጂዎችን አባዝቶ ማቅረብ፤

፫/ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን ለማዘመን እና ውጤታማ ለማድረግ አቅም መገንባት፣

## ፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት የግብርና ምርምር ያከናውናል እንዲሁም እንዲከናወን ያደርጋል፤

፪/ ከአገራዊ የግብርና ልማት ፖሊሲ ጋር የተጣጣሙ የግብርና ምርምር ስትራቴጅዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፫/ ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ እና ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተባብራል፤

## 4. Head Office

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may have agricultural research centers elsewhere , as deemed necessary.

## 5. Objectives

The Institute shall have the following objectives:

1/ Generate, improve and adapt agricultural technologies and knowledge on plants, animals, soil and water addressing the needs of the agricultural development and the end users;

2/ Demonstrate agricultural research findings for users, multiply and provide source technologies;

3/ capacity building to Modernize and improve efficiency and effectiveness of the national agricultural research system.

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the following powers and duties to:

1/ Undertake and coordinate to undertake agricultural research in accordance with the national agricultural development policy and strategies;

2/ In harmonization with the National Agricultural Development Policy, develop the agricultural research strategies, programs and projects, and follow up the implementation of these;

3/ Establish and coordinate a system to develop and evaluate agricultural research programs and projects that meet the required national development needs;

፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ለሚቀርቡ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የመነሻ ቴክኖሎጅ ብዜት ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲባዛ ያደርጋል፤ ሂደቱንም ያስተባብራል፤

፭/ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ያማክራል፤

፮/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ በፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ገቢራዊ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፯/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ በማስፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ አመች በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የአህዝቦት ተግባር ያከናውናል፤

፰/ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የተመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ በመረጃ ቋት ያከማቻል፣ ያሰራጫል፣ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት ይገነባል፣ ይመራል፤

፱/ በግብርና ምርምር ተቋማትና የምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፲/ በግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት አቅም የማሳደግና የመገንባት ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ Establish a system for the production of source technologies, of improved Agricultural technologies provided by Agricultural research bodies multiply the source technologies and coordinate the process;

5/ Advise the government on agricultural research and development related policy issues;

6/ In collaboration with relevant stakeholders, establish functional system for creating strong partnerships among federal agricultural research centers and users for effective use of agricultural research technologies and follow up the implementation of it;

7/ In collaboration with relevant stakeholders, demonstrate research outputs through convenient and effective communication media and local languages to enhance the agricultural knowledge base of the public;

8/ Collect, collate, store and disseminate data and information related to agricultural research that are generated by the national research system and elsewhere, and establish a system for agricultural research data or information exchange mechanism;

9/ Organize functional platforms for promoting strong linkages among agricultural research institutions, consumers, and other value chain actors;.

10/ Design the development and upgrading of skilled and qualified human resources engaged in agricultural research; formulate and implement effective strategies to develop and build up human capacity;

፲፩/ የግብርና ምርምር ተቋማት ዘመናዊ የምርምር መሠረተ ልማትን እና የምርምር መሣሪያዎች ሳይንሳዊ ደረጃን የጠበቁ እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤ የምርምር ሥርዓቱ አካላት በቅንጅት የሚጠቀሙበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፪/ በሥሩ የሚተዳደሩ የግብርና ምርምር ማዕከላት እንደገና እንዲደራጁ፣ እንዲታጠፉ እና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ማዕከላት እንዲቋቋሙ የሚያስችል ጥናት በማድረግ በሚኒስቴሩ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ የግብርና ምርምር ማዕከላትን በብቃት ደረጃ መለኪያ መስፈርቶች መሰረት ያስገመግማል፣ የልህቀት ማዕከልነት ዕውቅና እንዲሰጥ ያመቻቻል፤

፲፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ጠቃሚ ውጤቶችን ላስመዘገቡ ሰዎች ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፭/ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አገራዊ ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት ይመሰርታል፣ ስምምነቶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲፮/ በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያ ማህበራት ያበረታታል እንዲሁም ለግብርና ምርምር በመረጃ ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፯/ የግብርና ምርምር በሚያከናውኑ ተቋማት መካከል አስፈላጊ ያልሆነ የምርምር ድግግሞሽን በማስቀረት የምርምር ሥርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

11/ Establish an effective and efficient research infrastructures and equipment in conformity with scientific and international standards; create mechanisms to utilize the same resources by the agricultural research system collaboratively;

12/ Reorganize or dissolve any research center under the institute and establish new ones as deemed necessary through conduct study and implement as approved by the government;

13/ Based on standard quality measurement criteria's, it works to certify the competence of research centers in the national agricultural research system, and facilitate for excellence of research centers;

14/ Establish an award and recognition system to individuals or entities for meritorious achievements in the national agricultural research system;

15/ establish strategic partnership with relevant international and regional Agricultural research institutes and national Organizations having similar objective, signs agreements and implement thereof;

16/ Encourage agricultural professional associations and facilitate their contribution for the exchange of agricultural research knowledge and information;

17/ Establish a workable system to minimize duplication of research efforts thereby enhance efficiency and effectiveness of the agricultural research system;

፲፰/ የግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ምርምር ማካሄድ ለሚፈልጉ የአገር ውስጥና የውጭ የምርምር ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግብርና ምርምር ለማካሄድ የሚያስችል ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፱/ ከምርምር ሥርዓቱ ለሚወጡና የላቀ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ቴክኖሎጂዎች እና ዕውቀቶች የአዕምሮአዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

፳፩/ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችሉ ተቋማዊ የአፈፃፀም መለኪያዎችና አሰራሮችን ያዘጋጃል፤

፳፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፳፫/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተር፤

፪/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰. የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ኢንስቲትዩቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

18/ Support foreign and local research institutions and individuals intending to undertake agricultural research in line with agricultural policies and strategies of the country;

19/ Facilitate the acquisition of ownership of intellectual property rights for technologies, knowledge, process and information generated by the agricultural research system;

20/ Collect service fee based on a rate set by a Regulation to be issued by Council of Ministers.

21/ Prepare institutional implementation standardes and practices that would help to implement its mission.

22/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

23/ Perform other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

## 7. Organizational Structure

The institute shall have:

1/ A Director General;

2/ Deputy Director Generals as required; and

3/ Necessary staffs.

## 8. Powers and Duties of the Director General

The Director General shall have the following powers and duties:

1/ The Director General shall be the Chief Executive Officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute;

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ሥር የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትን የፕሮግራምና የፕሮጀክት አፈጻጸም፤ የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤

ሐ) አግባብነት ባላቸው በፌደራል መንግሥት የሠራተኞች ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶና አጠናቅሮ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በጸደቀው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ለምርምር ማዕከላት እና በቅንጅት ለሚሰሩ ስራዎች ይመድባል፤ የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፡

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስፈላጊነቱ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2/ Without limiting the generality provided in Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Implement the powers and responsibilities of the Institute provided in Article 6 of this Regulation;

b) Supervise and follow up the implementation of programs and projects as well as the utilization of finance by the federal agricultural research centers;

c) Recruit and administer staff of the institute based on the Civil Service Laws of the Country;

d) Prepare, consolidate and submit the work program and budget of the institute to the government and follow up its proper implementation when approved;

e) Allocate budget to research centers based on the approved budget of the institute and follow up the utilization of the allocated fund for the intended activity;

f) Represent the institute in its dealings with third parties;

g) Consolidate the performance and financial report of the institute, and submit to the Ministry.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

**፱. የምክትል ዋና ዳሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

**፲. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

**፲፩. ስለሂሣብ መዝገብ**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብቱን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡

**፲፪. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**9. Powers and Duties of the Deputy Director General**

The Deputy Director General shall have the following powers and duties:

1/ Assist the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the activities of the institute;

2/ Execute other duties specifically assigned by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise , the Senior Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence

**10. Budget of the Institute**

The budget of the Institute shall be allocated by the Government.

**11. Book of Accounts**

1/ The Institute shall keep a complete and an accurate book of accounts.

2/ The Institute book of accounts shall be audited at least once a year by the Auditor General or by another Auditor designated by him.

**12. Inapplicable Laws**

Any other Regulations, Directives or Customary Practices which are in contradiction with this Regulation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

## ፲፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 13. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette

**Done at Addis Ababa, on this 13th day of December, /2022**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.6
ADDIS ABABA 13th December, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፳፻፲፭

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ……………………………………..ገጽ ፲፬ሺ፭፻፺

## Content

Regulation No. 527/2022

The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation ……..........................................................Page 14590

**ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፳፻፲፭**

**የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፳፻፲፬ አንቀጽ ፩፻፫ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፳፻፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ወስጥ፡-

፩/ **“የግብርና ምርምር”** ማለት የዕጽዋት፣ የእንስሳት፣ አፈርና ውኃ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚከናወን ሳይንሳዊ ተግባር ነው፤

**Regulation No. 527/2022**

**THE ETHIOPIAN INSTITUTE OF AGRICULTURAL RESEARCH ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2023.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as “ The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation Number 527/2022”

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ **“Agricultural research”** means an undertaking to advance production, productivity and quality products in the areas of plants, animals, and soil and water resources in a sustainable manner;

፪/ **"የግብርና ምርምር ሥርዓት"** ማለት በአገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርምር የተሰማሩ ተቋማት በጋራ ወይም በጣምራ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር በሚያገናኙዋቸው ጉዳዮች ላይ የሚመሰርቱት የተዋረድ ወይም የጎንዮሽ ግንኙነት ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚመሩበትን መርሆዎች እና አሰራሮችን የሚያካትት ነው፤

፫/ **"የግብርና ምርምር ማዕከል"** ማለት በፌደራል መንግሥት ወይም በክልል መስተዳድር የሚተዳደር ሆኖ ሥነ-ምህዳርን ወይም የማሕበረሰብ ተደራሽነትን ወይም የግብርና ምርት ዓይነትን ወይም የትኩረት መስክን ታሳቢ አድርጎ የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም የግብርና ምርምር ተግባራትን የሚያከናውን አካል ነው፤

፬/ **"ቴክኖሎጂ"** ማለት አዲስ ወይም የተሻሻለ ወይም የተላመደ የግብርና ምርት ዓይነት፣ አመራረትና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተጣመረ ዕውቀት፣ የድርጊት ጥበብ፣ የአሰራር ዘዴና ሥርዓት ሆኖ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ማነቆዎችን ለመፍታትና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችል ወይም ለዚህ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው፤

፭/ **"ዕውቀት"** ማለት በጥናትና ምርምር የሚገኝ ቴክኒክ፣ ክህሎት፣ ዘዴ፣ ጥበብን እና የአሰራር ሂደቶችን የሚያጠቃልል ሆኖ አንድን የግብርና ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ወይም የምርምር ዓላማን ለማሳካት የሚያስችል ጽንሰ ሃሳብ ነው፤

፮/ **"ማስተባበር"** ማለት የአገራዊ የግብርና ምርምር ስራዎች በቅንጅት፣ በትብብርና በውጤታማነት እንዲከናወኑ የማሳለጥ ተግባር ነው፤

2/ **"National Agricultural Research System"** means a collection of institutions engaged in the agricultural research within the country and doing research in harmony or in collaboration, having vertical or horizontal relationships with governing principles and working modalities;

3/ **"Agricultural Research Center"** means an agricultural research organ entirely dedicated in implementing research activities and projects; established or to be established or administered by Federal or Regional government to address agro-ecologies, social groups, or strategic commodities or strategic themes;

4/ "**Technology**" means new or improved or adapted product type and knowledge in agriculture that embedded with the provision of production and services, wisdom, working method and system that could solve the social and economic bottlenecks and improve the living conditions of the farming society or contributing to these;

5/ "**Knowledge**" means the sum of techniques, skills, methods, wisdoms and processes to be employed in the production of goods or services or in the accomplishment of objectives, such as scientific investigations;

6/ "**Coordination**" Means facilitating agricultural research endeavorsare conducted collaboratively to enhance efficiency and synergy;

፯/ "**አገልግሎት**" ማለት በኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ማንኛውም የስልጠና፣ የማማከርና ጥናት፣ የቤተ-ሙከራ ናሙና ፍተሻና ትንተና፣ በመስክና በቤተ-ሙከራ የቴክኖሎጂ ውጤታማነት ማረጋገጥ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በውል አማካይነት የሚከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፤

፰/ "**ተቋም**" ማለት የግብርና ምርምርን እንዲያካሂድ በሕግ የተፈቀደለት የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት አካል ወይም መንግስታዊ የልማት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

፱/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፩/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>መቋቋም</u>

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌደራል አስፈፃሚ ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**7/** "**Service**" means the provision of training, consultancy, laboratory testing, validating technologies in laboratories and under field conditions, and other similar activities that emanate from the competences of the institute or its missions that may be provided on contractual basis;

**8/** "**Institution**" means any Organization authorized to work on agricultural research at federal or regional level, at Universities or Colleges or government or private entities;

**9/** **"Region"** means any state established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and including the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrations;

**10/** "Ministry or Minister" means the Ministry of Agriculture or the Minister, respectively;

**11/** "**Person**" means physical or juridical person;

**12/** Any expression in masculine gender includes the feminine

## 3. <u>Establishment</u>

The Ethiopian Institute of Agricultural Research (hereinafter the "Institute'') is hereby established as a Federal Government Institution.

**፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ሥፍራዎች የግብርና ምርምር ማዕከላት ይኖሩታል፡፡

**፭. <u>ዓላማ</u>**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት እና በተጠቃሚዎች ፍላጎቶች ላይ ያተኮሩ በዕጽዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈርና ውኃ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና ዕውቀቶችን ማፍለቅ፣ ማሻሻልና ማላመድ፤

፪/ የግብርና ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ እና የመነሻ ቴክኖሎጂዎችን አባዝቶ ማቅረብ፤

፫/ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን ለማዘመን እና ውጤታማ ለማድረግ አቅም መገንባት፣

**፮. <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት የግብርና ምርምር ያከናውናል እንዲሁም እንዲከናወን ያደርጋል፤

፪/ ከአገራዊ የግብርና ልማት ፖሊሲ ጋር የተጣጣሙ የግብርና ምርምር ስትራቴጅዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፫/ ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ እና ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተባብራል፤

**4. <u>Head Office</u>**

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may have agricultural research centers elsewhere , as deemed necessary.

**5. <u>Objectives</u>**

The Institute shall have the following objectives:

1/ Generate, improve and adapt agricultural technologies and knowledge on plants, animals, soil and water addressing the needs of the agricultural development and the end users;

2/ Demonstrate agricultural research findings for users, multiply and provide source technologies;

3/ capacity building to Modernize and improve efficiency and effectiveness of the national agricultural research system.

**6. <u>Powers and Duties of the Institute</u>**

The Institute shall have the following powers and duties to:

1/ Undertake and coordinate to undertake agricultural research in accordance with the national agricultural development policy and strategies;

2/ In harmonization with the National Agricultural Development Policy, develop the agricultural research strategies, programs and projects, and follow up the implementation of these;

3/ Establish and coordinate a system to develop and evaluate agricultural research programs and projects that meet the required national development needs;

፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ለሚቀርቡ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የመነሻ ቴክኖሎጅ ብዜት ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲባዛ ያደርጋል፤ ሂደቱንም ያስተባብራል፤

፭/ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ያማክራል፤

፮/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ በፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ገቢራዊ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፯/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ በማስፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ አመች በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የአህዝቦት ተግባር ያከናውናል፤

፰/ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የተመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ በመረጃ ቋት ያከማቻል፣ ያሰራጫል፣ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት ይገነባል፣ ይመራል፤

፱/ በግብርና ምርምር ተቋማትና የምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፲/ በግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት አቅም የማሳደግና የመገንባት ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ Establish a system for the production of source technologies, of improved Agricultural technologies provided by Agricultural research bodies multiply the source technologies and coordinate the process;

5/ Advise the government on agricultural research and development related policy issues;

6/ In collaboration with relevant stakeholders, establish functional system for creating strong partnerships among federal agricultural research centers and users for effective use of agricultural research technologies and follow up the implementation of it;

7/ In collaboration with relevant stakeholders, demonstrate research outputs through convenient and effective communication media and local languages to enhance the agricultural knowledge base of the public;

8/ Collect, collate, store and disseminate data and information related to agricultural research that are generated by the national research system and elsewhere, and establish a system for agricultural research data or information exchange mechanism;

9/ Organize functional platforms for promoting strong linkages among agricultural research institutions, consumers, and other value chain actors;.

10/ Design the development and upgrading of skilled and qualified human resources engaged in agricultural research; formulate and implement effective strategies to develop and build up human capacity;

፲፩/ የግብርና ምርምር ተቋማት ዘመናዊ የምርምር መሠረተ ልማትን እና የምርምር መሣሪያዎች ሳይንሳዊ ደረጃን የጠበቁ እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤ የምርምር ሥርዓቱ አካላት በቅንጅት የሚጠቀሙበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፪/ በሥሩ የሚተዳደሩ የግብርና ምርምር ማዕከላት እንደገና እንዲደራጁ፣ እንዲታጠፉ እና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ማዕከላት እንዲቋቋሙ የሚያስችል ጥናት በማድረግ በሚኒስቴሩ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ የግብርና ምርምር ማዕከላትን በብቃት ደረጃ መለኪያ መስፈርቶች መሰረት ያስገመግማል፣ የልህቀት ማዕከልነት ዕውቅና እንዲሰጥ ያመቻቻል፤

፲፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ጠቃሚ ውጤቶችን ላስመዘገቡ ሰዎች ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፭/ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አገራዊ ድርጅቶች ጋር ስትራቴጅካዊ አጋርነት ይመሰርታል፣ ስምምነቶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲፮/ በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያ ማህበራት ያበረታታል እንዲሁም ለግብርና ምርምር በመረጃ ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፯/ የግብርና ምርምር በሚያከናውኑ ተቋማት መካከል አስፈላጊ ያልሆነ የምርምር ድግግሞሽን በማስቀረት የምርምር ሥርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

11/ Establish an effective and efficient research infrastructures and equipment in conformity with scientific and international standards; create mechanisms to utilize the same resources by the agricultural research system collaboratively;

12/ Reorganize or dissolve any research center under the institute and establish new ones as deemed necessary through conduct study and implement as approved by the government;

13/ Based on standard quality measurement criteria's, it works to certify the competence of research centers in the national agricultural research system, and facilitate for excellence of research centers;

14/ Establish an award and recognition system to individuals or entities for meritorious achievements in the national agricultural research system;

15/ establish strategic partnership with relevant international and regional Agricultural research institutes and national Organizations having similar objective, signs agreements and implement thereof;

16/ Encourage agricultural professional associations and facilitate their contribution for the exchange of agricultural research knowledge and information;

17/ Establish a workable system to minimize duplication of research efforts thereby enhance efficiency and effectiveness of the agricultural research system;

፲፰/ የግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ምርምር ማካሄድ ለሚፈልጉ የአገር ውስጥና የውጭ የምርምር ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግብርና ምርምር ለማካሄድ የሚያስችል ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፱/ ከምርምር ሥርዓቱ ለሚወጡና የላቀ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ቴክኖሎጂዎች እና ዕውቀቶች የአዕምሮአዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

፳፩/ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችሉ ተቋማዊ የአፈፃፀም መለኪያዎችና አሰራሮችን ያዘጋጃል፤

፳፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፳፫/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተር፤

፪/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰. የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ኢንስቲትዩቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

18/ Support foreign and local research institutions and individuals intending to undertake agricultural research in line with agricultural policies and strategies of the country;

19/ Facilitate the acquisition of ownership of intellectual property rights for technologies, knowledge, process and information generated by the agricultural research system;

20/ Collect service fee based on a rate set by a Regulation to be issued by Council of Ministers.

21/ Prepare institutional implementation standardes and practices that would help to implement its mission.

22/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

23/ Perform other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

## 7. Organizational Structure

The institute shall have:

1/ A Director General;

2/ Deputy Director Generals as required; and

3/ Necessary staffs.

## 8. Powers and Duties of the Director General

The Director General shall have the following powers and duties:

1/ The Director General shall be the Chief Executive Officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute;

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ሥር የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትን የፕሮግራምና የፕሮጀክት አፈጻጸም፤ የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤

ሐ) አግባብነት ባላቸው በፌደራል መንግሥት የሠራተኞች ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶና አጠናቅሮ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በጸደቀው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ለምርምር ማዕከላት እና በቅንጅት ለሚሰሩ ስራዎች ይመድባል፤ የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፡

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስፈላጊነቱ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2/ Without limiting the generality provided in Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Implement the powers and responsibilities of the Institute provided in Article 6 of this Regulation;

b) Supervise and follow up the implementation of programs and projects as well as the utilization of finance by the federal agricultural research centers;

c) Recruit and administer staff of the institute based on the Civil Service Laws of the Country;

d) Prepare, consolidate and submit the work program and budget of the institute to the government and follow up its proper implementation when approved;

e) Allocate budget to research centers based on the approved budget of the institute and follow up the utilization of the allocated fund for the intended activity;

f) Represent the institute in its dealings with third parties;

g) Consolidate the performance and financial report of the institute, and submit to the Ministry.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

## ፱. የምክትል ዋና ዳሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፲. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

## ፲፩. ስለሂሣብ መዝገብ

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብቱን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡

## ፲፪. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 9. Powers and Duties of the Deputy Director General

The Deputy Director General shall have the following powers and duties:

1/ Assist the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the activities of the institute;

2/ Execute other duties specifically assigned by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise , the Senior Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence

## 10. Budget of the Institute

The budget of the Institute shall be allocated by the Government.

## 11. Book of Accounts

1/ The Institute shall keep a complete and an accurate book of accounts.

2/ The Institute book of accounts shall be audited at least once a year by the Auditor General or by another Auditor designated by him.

## 12. Inapplicable Laws

Any other Regulations, Directives or Customary Practices which are in contradiction with this Regulation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

## ፲፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 13. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette

**Done at Addis Ababa, on this 13th day of December, /2022**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.6
ADDIS ABABA 13th December, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፪ሺ፲፭

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ……………………………………..ገጽ ፲፬ሺ፭፻፺

## Content

Regulation No. 527/2022

The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation ……...........................................................Page 14590

**ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፪ሺ፲፭**

## የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፩፻፫ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፳፯/፪ሺ፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ **“የግብርና ምርምር”** ማለት የዕጽዋት፣ የእንስሳት፣ አፈርና ውኃ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚከናወን ሳይንሳዊ ተግባር ነው፤

**Regulation No. 527/2022**

## THE ETHIOPIAN INSTITUTE OF AGRICULTURAL RESEARCH ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2023.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as “ The Ethiopian Institute of Agricultural Research Establishment Council of Ministers Regulation Number 527/2022”

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ **“Agricultural research”** means an undertaking to advance production, productivity and quality products in the areas of plants, animals, and soil and water resources in a sustainable manner;

፪/ **“የግብርና ምርምር ሥርዓት”** ማለት በአገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርምር የተሰማሩ ተቋማት በጋራ ወይም በጣምራ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር በሚያገናኙዋቸው ጉዳዮች ላይ የሚመሰርቱት የተዋረድ ወይም የጎንዮሽ ግንኙነት ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚመሩበትን መርሆዎች እና አሰራሮችን የሚያካትት ነው፤

2/ **“National Agricultural Research System”** means a collection of institutions engaged in the agricultural research within the country and doing research in harmony or in collaboration, having vertical or horizontal relationships with governing principles and working modalities;

፫/ **“የግብርና ምርምር ማዕከል”** ማለት በፌደራል መንግሥት ወይም በክልል መስተዳድር የሚተዳደር ሆኖ ሥነ-ምህዳርን ወይም የማሕበረሰብ ተደራሽነትን ወይም የግብርና ምርት ዓይነትን ወይም የትኩረት መስክን ታሳቢ አድርጎ የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም የግብርና ምርምር ተግባራትን የሚያከናውን አካል ነው፤

3/ **"Agricultural Research Center"** means an agricultural research organ entirely dedicated in implementing research activities and projects; established or to be established or administered by Federal or Regional government to address agro-ecologies, social groups, or strategic commodities or strategic themes;

፬/ **"ቴክኖሎጂ"** ማለት አዲስ ወይም የተሻሻለ ወይም የተላመደ የግብርና ምርት ዓይነት፣ አመራረትና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተጣመረ ዕውቀት፣ የድርጊት ጥበብ፣ የአሰራር ዘዴና ሥርዓት ሆኖ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ማነቆዎችን ለመፍታትና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያስችል ወይም ለዚህ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው፤

4/ “**Technology**” means new or improved or adapted product type and knowledge in agriculture that embedded with the provision of production and services, wisdom, working method and system that could solve the social and economic bottlenecks and improve the living conditions of the farming society or contributing to these;

፭/ **“ዕውቀት”** ማለት በጥናትና ምርምር የሚገኝ ቴክኒክ፣ ክህሎት፣ ዘዴ፣ ጥበብን እና የአሰራር ሂደቶችን የሚያጠቃልል ሆኖ አንድን የግብርና ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ወይም የምርምር ዓላማን ለማሳካት የሚያስችል ጽንሰ ሃሳብ ነው፤

5/ “**Knowledge**” means the sum of techniques, skills, methods, wisdoms and processes to be employed in the production of goods or services or in the accomplishment of objectives, such as scientific investigations;

፮/ **“ማስተባበር”** ማለት የአገራዊ የግብርና ምርምር ስራዎች በቅንጅት፣ በትብብርና በውጤታማነት እንዲከናወኑ የማሳለጥ ተግባር ነው፤

6/ “**Coordination**” Means facilitating agricultural research endeavorsare conducted collaboratively to enhance efficiency and synergy;

፯/ "**አገልግሎት**" ማለት በኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ማንኛውም የስልጠና፣ የማማከርና ጥናት፣ የቤተ-ሙከራ ናሙና ፍተሻና ትንተና፣ በመስክና በቤተ-ሙከራ የቴክኖሎጂ ውጤታማነት ማረጋገጥ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በውል አማካይነት የሚከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፤

፰/ "**ተቋም**" ማለት የግብርና ምርምርን እንዲያካሂድ በሕግ የተፈቀደለት የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት አካል ወይም መንግስታዊ የልማት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

፱/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፩/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>*መቋቋም*</u>

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌደራል አስፈፃሚ ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**7/** "**Service**" means the provision of training, consultancy, laboratory testing, validating technologies in laboratories and under field conditions, and other similar activities that emanate from the competences of the institute or its missions that may be provided on contractual basis;

**8/** "**Institution**" means any Organization authorized to work on agricultural research at federal or regional level, at Universities or Colleges or government or private entities;

**9/** **"Region"** means any state established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and including the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrations;

**10/** "Ministry or Minister" means the Ministry of Agriculture or the Minister, respectively;

**11/** "**Person**" means physical or juridical person;

**12/** Any expression in masculine gender includes the feminine

## 3. <u>Establishment</u>

The Ethiopian Institute of Agricultural Research (hereinafter the "Institute'') is hereby established as a Federal Government Institution.

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ሥፍራዎች የግብርና ምርምር ማዕከላት ይኖሩታል፡፡

**፭. ዓላማ**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት እና በተጠቃሚዎች ፍላጎቶች ላይ ያተኩሩ በዕጽዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈርና ውኃ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና ዕውቀቶችን ማፍለቅ፣ ማሻሻልና ማላመድ፤

፪/ የግብርና ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ እና የመነሻ ቴክኖሎጂዎችን አባዝቶ ማቅረብ፤

፫/ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን ለማዘመን እና ውጤታማ ለማድረግ አቅም መገንባት፣

**፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት የግብርና ምርምር ያከናውናል እንዲሁም እንዲከናወን ያደርጋል፤

፪/ ከአገራዊ የግብርና ልማት ፖሊሲ ጋር የተጣጣሙ የግብርና ምርምር ስትራቴጅዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፫/ ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ እና ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተባብራል፤

**4. Head Office**

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may have agricultural research centers elsewhere , as deemed necessary.

**5. Objectives**

The Institute shall have the following objectives:

1/ Generate, improve and adapt agricultural technologies and knowledge on plants, animals, soil and water addressing the needs of the agricultural development and the end users;

2/ Demonstrate agricultural research findings for users, multiply and provide source technologies;

3/ capacity building to Modernize and improve efficiency and effectiveness of the national agricultural research system.

**6. Powers and Duties of the Institute**

The Institute shall have the following powers and duties to:

1/ Undertake and coordinate to undertake agricultural research in accordance with the national agricultural development policy and strategies;

2/ In harmonization with the National Agricultural Development Policy, develop the agricultural research strategies, programs and projects, and follow up the implementation of these;

3/ Establish and coordinate a system to develop and evaluate agricultural research programs and projects that meet the required national development needs;

፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ለሚቀርቡ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የመነሻ ቴክኖሎጅ ብዜት ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲባዛ ያደርጋል፤ ሂደቱንም ያስተባብራል፤

፭/ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ያማክራል፤

፮/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ በፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ገቢራዊ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፯/ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ በማስፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ አመች በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችና በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የአህዝቦት ተግባር ያከናውናል፤

፰/ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የተመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ በመረጃ ቋት ያከማቻል፣ ያሰራጫል፣ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት ይገነባል፣ ይመራል፤

፱/ በግብርና ምርምር ተቋማትና የምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፲/ በግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት አቅም የማሳደግና የመገንባት ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ Establish a system for the production of source technologies, of improved Agricultural technologies provided by Agricultural research bodies multiply the source technologies and coordinate the process;

5/ Advise the government on agricultural research and development related policy issues;

6/ In collaboration with relevant stakeholders, establish functional system for creating strong partnerships among federal agricultural research centers and users for effective use of agricultural research technologies and follow up the implementation of it;

7/ In collaboration with relevant stakeholders, demonstrate research outputs through convenient and effective communication media and local languages to enhance the agricultural knowledge base of the public;

8/ Collect, collate, store and disseminate data and information related to agricultural research that are generated by the national research system and elsewhere, and establish a system for agricultural research data or information exchange mechanism;

9/ Organize functional platforms for promoting strong linkages among agricultural research institutions, consumers, and other value chain actors;.

10/ Design the development and upgrading of skilled and qualified human resources engaged in agricultural research; formulate and implement effective strategies to develop and build up human capacity;

፲፩/ የግብርና ምርምር ተቋማት ዘመናዊ የምርምር መሠረተ ልማትን እና የምርምር መሣሪያዎች ሳይንሳዊ ደረጃን የጠበቁ እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤ የምርምር ሥርዓቱ አካላት በቅንጅት የሚጠቀሙበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፪/ በሥሩ የሚተዳደሩ የግብርና ምርምር ማዕከላት እንደገና እንዲደራጁ፣ እንዲታጠፉ እና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ማዕከላት እንዲቋቋሙ የሚያስችል ጥናት በማድረግ በሚኒስቴሩ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ የግብርና ምርምር ማዕከላትን በብቃት ደረጃ መለኪያ መስፈርቶች መሰረት ያስገመግማል፣ የልህቀት ማዕከልነት ዕውቅና እንዲሰጥ ያመቻቻል፤

፲፬/ በግብርና ምርምር ሥርዓቱ ጠቃሚ ውጤቶችን ላስመዘገቡ ሰዎች ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፭/ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አገራዊ ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት ይመሰርታል፣ ስምምነቶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲፮/ በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያ ማህበራት ያበረታታል እንዲሁም ለግብርና ምርምር በመረጃ ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፯/ የግብርና ምርምር በሚያከናውኑ ተቋማት መካከል አስፈላጊ ያልሆነ የምርምር ድግግሞሽን በማስቀረት የምርምር ሥርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

11/ Establish an effective and efficient research infrastructures and equipment in conformity with scientific and international standards; create mechanisms to utilize the same resources by the agricultural research system collaboratively;

12/ Reorganize or dissolve any research center under the institute and establish new ones as deemed necessary through conduct study and implement as approved by the government;

13/ Based on standard quality measurement criteria's, it works to certify the competence of research centers in the national agricultural research system, and facilitate for excellence of research centers;

14/ Establish an award and recognition system to individuals or entities for meritorious achievements in the national agricultural research system;

15/ establish strategic partnership with relevant international and regional Agricultural research institutes and national Organizations having similar objective, signs agreements and implement thereof;

16/ Encourage agricultural professional associations and facilitate their contribution for the exchange of agricultural research knowledge and information;

17/ Establish a workable system to minimize duplication of research efforts thereby enhance efficiency and effectiveness of the agricultural research system;

፲፰/ የግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ምርምር ማካሄድ ለሚፈልጉ የአገር ውስጥና የውጭ የምርምር ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግብርና ምርምር ለማካሄድ የሚያስችል ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፱/ ከምርምር ሥርዓቱ ለሚወጡና የላቀ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ቴክኖሎጂዎች እና ዕውቀቶች የአዕምሮአዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፳/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

፳፩/ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችሉ ተቋማዊ የአፈፃፀም መለኪያዎችና አሰራሮችን ያዘጋጃል፣

፳፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፳፫/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተር፣

፪/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰. <u>የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ኢንስቲትዩቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

18/ Support foreign and local research institutions and individuals intending to undertake agricultural research in line with agricultural policies and strategies of the country;

19/ Facilitate the acquisition of ownership of intellectual property rights for technologies, knowledge, process and information generated by the agricultural research system;

20/ Collect service fee based on a rate set by a Regulation to be issued by Council of Ministers.

21/ Prepare institutional implementation standardes and practices that would help to implement its mission.

22/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

23/ Perform other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

## 7. <u>Organizational Structure</u>

The institute shall have:

1/ A Director General;

2/ Deputy Director Generals as required; and

3/ Necessary staffs.

## 8. <u>Powers and Duties of the Director General</u>

The Director General shall have the following powers and duties:

1/ The Director General shall be the Chief Executive Officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute;

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ሥር የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትን የፕሮግራምና የፕሮጀክት አፈጻጸም፤ የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤

ሐ) አግባብነት ባላቸው በፌደራል መንግሥት የሠራተኞች ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶና አጠናቅሮ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በጸደቀው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ለምርምር ማዕከላት እና በቅንጅት ለሚሰሩ ስራዎች ይመድባል፤ የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፡

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስፈላጊነቱ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2/ Without limiting the generality provided in Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Implement the powers and responsibilities of the Institute provided in Article 6 of this Regulation;

b) Supervise and follow up the implementation of programs and projects as well as the utilization of finance by the federal agricultural research centers;

c) Recruit and administer staff of the institute based on the Civil Service Laws of the Country;

d) Prepare, consolidate and submit the work program and budget of the institute to the government and follow up its proper implementation when approved;

e) Allocate budget to research centers based on the approved budget of the institute and follow up the utilization of the allocated fund for the intended activity;

f) Represent the institute in its dealings with third parties;

g) Consolidate the performance and financial report of the institute, and submit to the Ministry.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

**፱. የምክትል ዋና ዳሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

**፲. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

**፲፩. ስለሂሣብ መዝገብ**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብቱን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡

**፲፪. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**9. Powers and Duties of the Deputy Director General**

The Deputy Director General shall have the following powers and duties:

1/ Assist the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the activities of the institute;

2/ Execute other duties specifically assigned by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise , the Senior Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence

**10. Budget of the Institute**

The budget of the Institute shall be allocated by the Government.

**11. Book of Accounts**

1/ The Institute shall keep a complete and an accurate book of accounts.

2/ The Institute book of accounts shall be audited at least once a year by the Auditor General or by another Auditor designated by him.

**12. Inapplicable Laws**

Any other Regulations, Directives or Customary Practices which are in contradiction with this Regulation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

## ፲፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 13. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette

**Done at Addis Ababa, on this 13th day of December, /2022**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**